የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)

SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

**ጥቅምት 7/ 2010 ዓ.ም.**

# ***<u>ዘገባ</u>***

## *<u>በቦረና አካባቢ በዜጎች ላይ የተፈጸሙ አንዳንድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች</u>*

የሚከተለው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አጭር ጥንቅር በዝርዝርና የተሟላ መረጃና ማስረጃ የተደገፈ አይደለም:: ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት የአቅም ማነስ ነው:: የጥንቅሩ ዋና ዓላማ ጉዳዩ የሚያሳስባቸው ወገኖች ሁሉ ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ አድርገው ችግሩን ለማጋለጥ ይነሳሱ ዘንድ የመነሻ ጥቆማ ማቅረብ ብቻ ነው::

1) በቦረና ዞን በሀገረ ማርያም ከተማ ለእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች በተከለለ የመቃብር ሥፍራ ውስጥ አንድ ሰው በ 02/13/2002 ዓ.ም. ተሰቅሎ ተገኝቷል:: የሰውየውን ማንነት ማወቅ አልተቻለም:: ነገር ግን የለበሰው ልብስ፤ ቀበቶና ካልሲው ውድ ዋጋ ያላቸው መሆኑን የአይን እማኞች አረጋግጠዋል:: ምናልባትም የከተማ ሰው ሣይሆን እንደማይቀር ይገምታሉ::

እንደ አይን እማኞቹ ገለጻ ከሆነ በአካላቱ ላይ ያሉ ምልክቶች ሰውየው ተደብድቦ የተሰቀለ መሆኑን ይጠቁማሉ:: በተለይም ሁለቱም ዓይኖቹ የወጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል:: አስከሬኑ ለምርመራ ሐኪም ቤት እንዳይሄድና ስለጉዳዩ ሕጋዊ ክትትል እንዳይደረግም ጥድፊያ የተሞላበት የክልከላና የማድበስበስ ተግባር መፈጸሙም ታውቋል:: እነዚህና የመሳሰሉ ምልክቶችን ያስተዋሉት ምስክሮች ሰውየውን ምናልባት ከሌላ ሥፍራ አምጥተው ደብድበው ከገደሉት በኋላ ሳይሰቅሉት እንዳልቀረ ገምተዋል:: የአብዛኛው ነዋሪ ጥርጣሬም ተመሣሣይ እንደነበረ በወቅቱ በአካባቢው በስፋት ይሰማ ከነበረው ሁኔታ ለማወቅ ተችሏል::

በዚሁ ዞን በተለያዩ የገጠር መንደሮች፤ ከዚህ ቀደምም እንደዚሁ አንዳንድ በአካባቢው ነዋሪዎች የማይታወቁ ሰዎች አስከሬኖች ተጥለው ይገኙ እንደነበር ተጨምሮ ተገልጿል::

2) ከቦረና ዞን ከያቤሎ ከተማም ስማቸው ቀጥሎ የተዘረዘረው ስድስት ተማሪዎች ይህ ነው ተብሎ ባልተገለጸ ምክንያት ታስረዋል::

**2.1 መልቻ ሁቃ ከአብዳ ቀበሌ**

**2.2 ገልማ ዋሪዮ ከአርቦሮ ቀበሌ**

**2.3 ገልማ ቦከ ጨልካሲ ቀበሌ**

**2.4 ያተኔ ገርቦሌ ያቤሎ ዙሪያ**

**2.5 ሑቃ ጎዳና ያቤሎ ዙሪያ**

**2.6 ፋራ ገልገሎ ያቤሎ ዙሪያ**

ተማሪዎቹ በ24/12/2002 ዓ.ም. በያቤሎ ከተማ ደህንነቶች ተይዘው በቦረና ዞን ፖሊስ ጣቢያ እንዲታሰሩ ተደርጎ ነበር:: በማግሥቱ ቤተሰቦቻቸው ሊጠይቁ ወደ ጣቢያው ሲሄዱ ተማሪቹ በሥፍራው እንደሌሉ ተገልጾላቸዋል:: በኋላም ቤተሰብ ባደረገው ክትትል ተማሪዎቹ ወደ አዲስ አበባ ተወስደው ይህ መረጃ እስከሚዘጋጅበት የአሁኑ ሠዓት ድረስ በቃሊቲ እሥር ቤት እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል:: ከላይ የተገለጸውን ሁኔታ በመመልከት፤ ተማሪዎቹ የታሠሩት ከተቃውሞ ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው በሚባል ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መረዳት አያስቸግርም::

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE